# ቤት መልቀቅ

## ተከራዮች: መብቶችዎን ይወቁ!

**ምንም እንኳን የኪራይ ክፍያ ቢኖርቦት ወይም የኪራይ ውሎ ቢፈርስ አከራዮ ይህን ማድረግ አይችልም:**

| | | |
|---|---|---|
| ቤቱን እንዲለቁ የበር ቁልፎችን መቀየር | የቤቱ አገልግሎቶችን ማቋረጥ (መብራት, ውሃ, ጋዝ) | የሚመለከተው አካል ሳይመጣ የቤት እቃዎትን መንገድ ላይ አውጥቶ መጣል |

## ይህ ከደረሰቦት፣ ከመልቀቅዎት በፊት ስላሎት መብቶች ምክር ለማግኘት ይደውሉ

**የኪራይ ውል ከሌሎት፣ የውል ጊዜው ካለቀ፣ ወይም ውሉን ካፈረሱ የቤት አከራዮ ቤቱን እንዲለቁ ሊጠይቆት ይችላል**

**ከሚከተሉት አንዱን ከፈጸሙ የኪራይ ውል ሊያፈርሱ ይችላሉ**

- የኪራይ ክፍያን ካልከፈሉ ወይም ክፍያውን ከ5 ቀን በላይ ካዘገዩ
- በውሉ ላይ ያልተጠቀሰ ሰው አብሮት እየኖረ ከሆነ
- አደገኛ ነገር ለመፈጸም ካስፈራሩ ወይም ከፈጸሙ

## የኪራይ ውል አሎት? ይመልከቱ ! በነዚህ ተስማምተው ሊሆን ይችላል...

- "የጽሁፍ ማሳሰቢያ ተላልፏል" እንግዲያውስ የኪራይ ክፍያዎ ከ5 ቀናት በላይ ከዘገየ ባለንብረቱ **ያለማስጠንቀቂያ** ወደ ፍርድ ቤት ሊወስድዎት ይችላል።
- ቀድመው ከለቀቁ **ቅጣት** እንዲከፍሉ(ለምሳሌ የሁለት ወር የኪራይ ክፍያ)
- ቤቱን እንዲለቁ በህግ ከተወሰነቦት የኪራይ ክፍያ፣ የፍርድ ቤት ክፍያዎችን **እና** የአከራዩን የህግ አማካሪ ወጪ የመክፈል

የኪራይ ክፍያዎን ከከፈሉ ወይም ችግሩን ካስተካከሉ በውሉ ላይ በሰፈረው መሰረት ቤቱን መልቀቅል **ላይጠበቅብዎት ይችላል።**
**የማስጠንቀቂያው ቀን እስከሚጠናቀቅ ቤቱን ካለቀቁ ወይም ችግሩን ካላስተካከሉ፣**
**አከራዮ ወደ ፍርድ ቤት ሊወስዶት ይችላል።**

## ወደ ፍርድ ቤት ይሂዱ! ካልሆነ ግን አከራዮ ሙሉ ለሙሉ ያሸንፋል

## ወደ ፍርድ ቤት ሲሄዱ አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ

| | | |
|---|---|---|
| የህግ ባለሙያ ወይም አዲስ ቤት ለማግኘት ተጨማሪ ጊዜ ይፈልጋሉ? **ዳኛውን** የሁለት ሳምንት ማራዘሚያ **ይጠይቁ**። ዳኛው የፍርድ ቤት ቀጠሮዎን ለማራዘም ሊስማሙ ይችላሉ። | የኪራይ ክፍያውን አዘግይተው ከፍለው አከራዮት ወስዶታል? **ለዳኛው** ደረሰኙን ወይም የተመለሰውን ቼክ **ያሳዩ**። ዳኛው ቤቱን እንዳይለቁ ሊያደርጎት ይችላል። | እንዲለቁ ምክንያት የነበረውን ችግር አስተካክለዋል? **ለዳኛው** ይህን ማድረጎን የሚያሳይ መረጃ **ያቅርቡ**። ዳኛው ቤቱን እንዳይለቁ ሊያደርጎት ይችላል። |

LEGAL AID SOCIETY OF MIDDLE TENNESSEE AND THE CUMBERLANDS (833) 837- የቤት

AMAC American Muslim Advisory Council (615) 988-6460

conexión américas (615) 701-7957

Nashville Hispanic Bar Association

**ይህ መረጃ ለዴቪድሰን ክልል ብቻ ነው።** እዚህ የቀረበው መረጃ የህግ ምክርን አይመሰርትም፤ ለመመስረት የታሰበም አይደለም። የሕግ ችግር ካጋጠመዎት፣ እባክዎን ለግል ጠበቃዎት ይደውሉ ወይም በአካባቢዎ የሚገኘውን የመካከለኛው ቴነሲ የሕግ ድጋፍ ማህበር እና የኩምበርላንድ ቢሮ በ1-800-238-1443 ወይም የናሽቪል የሂስፓኒክ ባር ማህበርን በ1-615-701-7957 ይደውሉ።

በ5/23 ተሻሽሏል።

# ከቤት የማስለቀቂያው ሂደት ምን ይመስላል?

**ማስታወሻ: ይህ የሚያገለግለው ለግል ተከራዮች ብቻ ነው። ለMDHA ወይም ለክፍል 8 የቤት ፕሮግራም ሂደቱ ከዚህ የተለየ ነው።**

## ቤቴን እንድለቅ የምደረገው ለምንድን ነው ?

### የክፍያ ቀን ማሳለፍ

የኪራይ ክፍያዎን ቀኑ ከደረሰ በኋላ **በአምስት ቀናት ውስጥ ካልከፈሉ** የቤቱ ባለቤት ከቤት የማስወጣት ሂደቱን መጀመር ይችላል። አከራዮ **የዘገየ የኪራይ ክፍያን መቀበል አይጠበቅበትም**።

### የውል ስምምነት መጣስ

እርስዎ ወይም እንግዳዎ **በውል ስምምነቱ ላይ ያልተፈቀደ ነገር ከፈጸሙ፣** የቤቱ ባለቤት እርስዎን ከቤቱ የማስወጣት ሂደቱን መጀመር ይችላል።

### የውል ጊዜ መጠናቀቅ

የኪራይ ውሎ **ቀነ ገደብ ከተጠናቀቀ** ወይም **የኪራይ ውል ከሌሎት፣** የቤቱ ባለቤት እርስዎን ከቤቱ የማስወጣት ሂደቱን **በምንም ዓይነት ምክንያት** መጀመር ይችላል።

## ከፍርድ ቤት በፊት ምን ያህል ጊዜ አለኝ?

ከዚህ በፊት ውል ካልነበሮት ወይም የኪራይ ውሎ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ካልተሰጠበት ለክፍያ **14 ቀናት** ይሰጦታል፤ ባለፉት 6 ወራት **ክፍያዎን አዘግይተው የሚያውቁ** ከሆነ ግን የሚሰጥዎት **የ 7 ቀናት ማስታወቂያ** ሲሆን **የመክፈል እድል የሎትም**።

**ውሎን ይመልከቱ! የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ለመቀበል ተስማምተው ከሆነ የቤቱ ባለቤት ይህንን ሂደት በመዝለል በቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት ሊወስዶት ይችላል።**

**ቢያንስ፣** አከራዮ በጽሁፍ የሚከተሉትን ሊሰጦት ይገባል:

- **የ3 ቀናት ማሳሰቢያ "ለጤና እና ለደህንነት አስጊ ለሆኑ ነገሮች"** (ለምሳሌ: አመጽ፣ ወንጀሎች)
- **የ14 ቀናት ማሳሰቢያ** ለተለያዩ ነገሮች ለምሳሌ ድምጽ ወይም የቤት አያያዝ። በውል ስምምነቱ ላይ ተገልጾ ከሆነ **ቤቱ ውስጥ መቆየት** ወይም **ችግሩን ማስተካከል** ይችሉ ይሆናል።

የቤት አከራዮ የቤት ኪራይ ከሚከፍሉበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ **የ30-ቀናት ማስታወቂያ** በጽሁፍ ሊሰጦት ይገባል።

## የማስታወቂያው ቀን ሲያበቃ ምን ማድረግ አለብኝ?

የማስታወቂያው ቀን ሲያበቃ, የቤቱ ባለቤት **መጥሪያ (ወደ ፍርድ ቤት ለመሄድ የሚሰጥ ማስታወቂያ)** ያስወጣል. **ለፍርድ ቤት ቀጠሮ ቢያንስ ከ6 ቀን በፊት** የመጥሪያው ቅጂ ሊደርሶት ይገባል። በአብዛኛው ጊዜ በመንግሥት ሰራተኛው ወይም በጉዳይ አስፈጻሚው ይመጣል። ነገር ግን ለመላክ ሞክረው ቤት ካልሆኑ በኢሜል መልእክት ሊመጣ ይችላል።

**መጥሪያ ከደረስዎት፣ ወደ ፍርድ ቤት ይሂዱ! የፍርድ ቤት ቀጠሮ ካለፎት አከራዮት ያሸንፋል፣ እርሶም ቤቶን ያጣሉ!**

## ወደ ፍርድ ቤት ስሄድ ምን ይፈጠራል?

ወደ ፍርድ ቤት ሲሄዱ፣ ለዳኛው እስከ **15 ቀን** ድረስ **የችሎቱን ቀን እንዲያራዝምሎት** "የይራዘምልኝ ጥያቄ" የማቅረብ መብት አለዎት። ይህንን ጊዜ **የህግ አማካሪ** ለማግኘት ወይም **የጎደለውን የኪራይ ክፍያ ይዞ ለመምጣት** ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

አከራዮ በፍርድ ቤት ቢያሸንፎትም ቤቱን እንዲለቁ ከመገደድዎ በፊት **በራስዎ እንዲወጡ 10 ቀናት** ይሰጥዎታል።

**ከ10 ቀናት በኋላ፣** የቤቱ ባለቤት "የማስለቀቂያ ትእዛዝ" ማግኘት ይችላል።ይህም የመንግሥት ተወካዮች ወደ ቤቱ እንዲመጡና አስገድደው እንዲያስወጡዎት እንዲሁም በቤቱ ውስጥ ያልዎትን ንብረትዎች በሙሉ እንዲያወጡ ይፈቅድላቸዋል። የመንግሥት ተወካዮች በአብዛኛው ጊዜ የሚመጡት የቤቱ ባለቤት ትእዛዙን ካስወጣ በኋላ ባለው **ከ 24 እስከ 48 ሰዓት** ጊዜ ውስጥ ነው።

LEGAL AID SOCIETY OF MIDDLE TENNESSEE AND THE CUMBERLANDS (833) 837-የቤት

AMAC American Muslim Advisory Council (615) 988-6460

conexión américas (615) 701-7957

Nashville Hispanic Bar Association

ይህ መረጃ ለዴቪድሰን ክልል ብቻ ነው። እዚህ የቀረበው መረጃ የህግ ምክርን አይመሰርትም፤ ለመመስረት የታሰበም አይደለም። የሕግ ችግር ካጋጠመዎት፣ እባክዎን ለግል ጠበቃዎት ይደውሉ ወይም በአካባቢዎ የሚገኘውን የመካከለኛው ቴነሲ የሕግ ድጋፍ ማህበር እና የኩምበርላንድ ቢሮ በ1-800-238-1443 ወይም የናሽቪል የሂስፓኒክ ባር ማህበርን በ1-615-701-7957 ይደውሉ።

በ5/23 ተሻሽሏል።